www.abyssinialaw.com

ነው፤ሊታረም ይገባዋል በማለት ጠይቋል፡፡ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ መልስና የመልስ መልስ በፅሁፍ አቅርበው እንዲከራከሩ አድርጓል፡፡

በዚህም መሠረት የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የፍትሐብሔሩን ህግ ቁጥር 1860(3) ጠቅሶ ጳጉሜ እንደወር አትቆጠርም የክሱ ጊዜ 6 ወር አልሞላውም ብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት እንደ ጭብጥ ቀርጿል፡፡

በመሆኑም የግራ ቀኙን ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካለው ህግ አኳያ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ የተጠቀሰው ሲሆን እኛም እንዳየነው አመልካች ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪ ያቀረቡት ከውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ ያቀረቡት ጥያቄ ጳጉሜ እንደወር ስለማትቆጠር 6ወር አልሞላም ተብሎ የይርጋ መቃወሚያው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውድቅ መደረጉና በፍሬ ነገሩ እንድንከራከር መደረጉ በአግባቡ አይደለም የሚል ነው፡፡ከመዝገቡ መገንዘብ እንደቻልነው አከራካሪ የሆነው የህግ ጥያቄ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 162(4) የሥራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሰራተኛውም ሆነ በአሰሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ ሥራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል የሚለው ድንጋጌ "ጳጉሜን ያካትታል ወይስ አያካትትም? በሚል ነጥብ ነው፡፡እንግዲህ ይርጋ ማለት የመብት ጥያቄ ጊዜ በማለፉ ቀሪ የሚሆንበት ነው ባንፃሩ መብት ላልነበረው የሚያጎናፅፍ ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የተጠሪ ጥያቄ በይርጋ አይቋረጥም የተባለበት ምክንያት የፍትሐብሔር ህጋችን አንቀፅ 1860(3) ጳጉሜን እንደወር ስለማይቆጥር እና የአሰሪና ሰራተኛ ህጉም "ወር"ን መሠረት አድርጎ ስለተደነገገ ነው፡፡

ጳጉሜ እንደ አስራ ሦስተኛ ወር የማትቆጠር መሆኑ ከታወቀ፣ የሀገራችን የአንድ አመት ጊዜ 12 ወራቶች ከሆኑ ከዚህ አቆጣጠር ውጭ ያሉት ቀናት በግራ ቀኙ መሀከል መብትም ሆነ ግዴታ ሊፈጥር አይገባም፡፡ጳጉሜ ተጠሪ ሥራም ላይ ቢሆኑ የሚሰጣቸው ጥቅም ወይም በመብት ደረጃ የሚጠይቁትም ክፍያ የለም፡፡እንግዲህ እንደወር የማይቆጠረው "ጊዜ" ለቀረበው ከውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ የሚነሣው የክፍያ ጥያቄ ጳጉሜ ተሰልቶ የተጠሪን መብት ሊያጣብብ አይገባውም፡፡

ባጠቃላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያውን ደረጃ ፍ/ቤት ብይን ሽሮ የተጠሪ ጥያቄ የ6ወር ይርጋ ጊዜ አላለፈበትም በማለት ወደ ሥር ፍ/ቤት መዝገቡን መመለሱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ብለናል፡፡በመሆኑም የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

www.abyssinialaw.com

# ው ሳ ኔ

1. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀን 4/8/05 በመ.ቁ.07615 የሰጠው ብይን ተሽሯል።
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀን 16/12/2005 በመ.ቁ.133056 የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል።
3. የግራ ቀኙ በፍሬ ነገር ደረጃ ክርክራቸው ይቀጥሉ ተብሎ በፍ/ብ/ስ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.341(1)መመለሱ በአግባቡ ነው ብለናል።
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራቸውን ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል፣ወደ መ/ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

እ/ኢ